# መጭውን ድል ለመተንበይ ካለፈው ስህተታችን መማር - በተለይም ከወረት ፖለቲካ መራቅ

ከሲሂራ

ሌላ ስህተት ላለመስራት ከተመክሮ በመማር እቅድ ማውጣትና የተተለመውን እቅድ ተግባራዊ ለማድረግ በጥንቃቄ መራመድን ይጠይቃል። ሲናገሩት ቀላል ነው ግን በተግባር ለማዋል ለዘመናት ስንቸገር ኑረናል። መጭውን የኢትዮጵያ ታሪክ መልካም ለማድረግ የሆያ ሆዬ ትግል መቅረት አለበት ማለት ብቻ ሳይሆን መኮነንም አለበት። የጎዳን የሞቅ ሞቅ ወረታዊ ትግል ስለመሆኑ አንዴ ብቻ ሳይሆን ደግመን ደጋግመን መናገር አለብን። በደንብ እስከሚዋጥልን ድረስ። የወረት ፍቅር አይዘልቅም የወረት ፖለቲካ ባጭር ከመቀጨቱም በላይ የህዝቡን ትግልም ያሽመደምዳል።

ባለሰሞነኛው ሞቅ ሞቅ ሊደደርገንና በወረት ፖለቲካ ሊጋልበን የመጣው ደግሞ ከእስር ቤት በቅርቡ የወጣው ስዬ አብርሃ ሆኗል። ይሄኛው ፖለቲካዊው የወረት ድራማ ካለፉት ለየት የሚያደርጉትን ጠባያት ተላብሷል። ለሳምንታት ብቅ ብለው ሊከስሙ የሚንፈራገጡትን ከዚህም ከዚያም ባንጀኛነት ድርጅታቸውን ሸሽተው የኮበለሉትን አሰባስቧል። ሃያ እንጃ ቢሰባሰብ አንድ ሃቀኛና ጠንካራ ድርጅት አይሆንም ምክንያቱም ሁሉም በመበተን ቈራ የረቀቀ እውቀት ስላላቸው የሃቀኛ ድርጅት መለያ የሆነውን መተማመን ሊኖራቸው አይችልም። የስልጣኑም ጥም በሁሉም ዘንድ የጎላ በመሆኑ እኔ ልምራ እኔ ልምራ በማለት ገና ከጅምሩ ከማያባራ ትግል ውስጥ ይገባሉ። በወረቱ የፖለቲካ ግለት ወቅት የማይናቅ ገንዘብ ከህዝብ መሰብሰባቸው አይቀርም። ባከፋፈሉ ሊታረቅ ከማይችሉበት ቅራኔ ውስጥም ይዘፈቃሉ አባቶቻችን እንደሚሉት ሌቦች ሲሰርቁ ይስማማሉ የሰረቁትን ሲከፋፈሉ ግን ይጣላሉ።

በርካታ የወረት ቴዎድሮሶችን ለመቁጠር ብንችልም ሃቀኛውን ቴዎድሮስ ያየነው በኢትዮጵያ ታሪክ መጽሃፍ ላይ ብቻ ነው። በርግጥ ወደፊት ታሪክ ውለታቸው የሚከፍላቸው በሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊ ቴዎድሮሶች በደርጉና በወያኔው ዘመን መፈጠራቸውን ሁላችንም የምናውቀው ሃቅ ነው። ለመማር የተሳነን ግን ብቅ የሚለውን አጭበርባሪ ሁሉ ተዌድሮስ ማድረጋችን ነው። በኢትዮጵያዊነታቸው የማያጠራጥሩ፣ ለጠላት የማያጎበድዱ፣ ለስልጣንና ለገንዘብ የማይንገበገቡ፣ በፖለቲካ ተመክሯቸው እጹብ ድንቅ ሊባሉ የሚገባቸው ግለሰቦች አይናችን ስር እያሉ፣ ለምን ለአበላ ባዩ እንደምንበለጥ ግራ የሚያጋብ ነው። ምናልባት በእጅ ያለ ወርቅ ከመዳብ ይቆጠራል ሆኖ ይሁን?

ከወያኔ አመጣጥ በፊት የነበረው የጠላትና የወዳጅ አሰላለፍ የመስታወት ያህል ግልጽ ነበር። ድንግርግራችን የወጣው ይህ ዘመነኛው ዘረኛ የሆነ መንግስት በጫንቃችን ላይ ከወጣበት ቀን አንድ ጀምሮ ነው። ወዳድንም ጠላንም ወያኔ የበለጠን በሃይል ብቻ ሳይሆን በማጭበርበር በፖለቲካም ተራቆብናል። ህዝቡን ማሳመንና እንዲወደው ማድረግ ቢሳነውም ከፋፍሎ መግዛቱን አውቆበታል። ቁጥራቸው የማይናቅም አለቅላቂዎችን እንደ ፍላጎታቸው ያስተንግዳቸዋል። ስልጣን ፈላጊውን ሚኒስቴር አድርጎ ያስለፈልፈዋል። ሆዳሙን ደግሞ በገንዘብ ወኔውን ሰልቦ በገዛ ወገኑ ላይ እንዲያሴር ያደርገዋ። ወያኔ ሊገባበት ባልቻለባቸው ድርጅቶች የፈጀውን ብር ይፍጅ የወሰደውን ጊዜም ይውሰድ ስርጎ-ገብ መስደድ ካቃተው በቀላሉ ሊበከሉ የሚችሉ ገርጋራ የድርጅቱን አባላት አባብሎ በገዛ ድርጅታቸው ላይ እንዲያሴሩ ያዘጋጃቸዋል። በቅንጅት፣ በህብረት አሁን ደግሞ በኢህአፓ ላይ የተከሰቱትን ያንጃ መፈጠር ማስተዋል በቂ ነው።

ወያኔን ለማብረክረክ በየስፍራው አለሁ ባዩ የተቃዋሚ ቁጥር ወኔ ቢኖረው ኑሮ ቀላል ድሮ ድሮ ወያኔን ማባረር በቻልን ነበር። የተቃዋሚው ጎራ በየድርጅቱ ውስጥ ስንት አባላት አዳካተተ ማወቅ ባይቻልም **አብዛኛዎቹ** ከትንሽ ኮሚቴ ቁጥር የማይበልጥ የአባላት ብዛት እንዳላቸው በርግጠኛነት መናገር ይቻላል። ምክር የሚቀበሉ ከሆነ አንዳንዶቹ እንዳደረጉት ከሚመስልላቸው ጋር ቢዋሃዱ ጥሩ ነው። አንጃዎቹ ደግሞ ለወራትም እንኳን የእድሜ ቋት እንዲኖራቸው የሰው ድርጅት ስም፡ ልሳን፡ ታሪክ፡ ለቀቅ ማድረግ ይገባቸውል። ሌላው ውንህደትን ሲሰብክ እነሱ ደግሞ መበታተንን ሲያሳዩ ተጠቃሚው ወያኔ እንጅ የኢትዮጵያ ህዝብ አለመሆኑን መሳት የለባቸውም። ሁለት ኢሕአፓ ሁለት ቅንጅት ሊኖር እንደማይችል ሕዝቡ አስምሮ ተናግሯል።

የልማድ አባባል ሳይሆን የአክብሮት ሆኖ ለተማረው ኢትዮጵያዊው ከፍተኝ የሆነ ከበሬታና አድንቆት አለን። በተለይም ያካበቱትን እውቀት መሳሪያ አድርገው ህዝቡን በማንቃት የአገሩን የወደፊት እድል ራሱ እንዲወስን እያስተማሩ ያሉቱን ምሁራን ምስጋና ይግባቸው። ያም ሆኖ ግን ገና ብዙ ይጠበቅባቸዋል።



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

አንዳንድ ምሁራን ደግሞ እናንተ ታገሉ እኔ ደግሞ መሪ እሆናለሁ ብለው እንደሚያስቡ መገመት ጥሩ ነው። የወያኔን አጥፊነት ለመረዳት ከምሁሩ ይልቅ ታትሮ ኗሪው ኢትዮጵያዊ በሚገባ ያውቀዋል። በርግጥ ያንዳንድ መሰረ ድርጅቶችንና ግለሰቦችን መሰረ ተንኮል ቦርቡሮ ማውጣትና ማጋለጥ ሃቀኛ ከሆነ ኢትዮጵያዊ ምሁር የሚጠበቅ ድርሻ ይሆናል። በርካታው ምሁር ግን ልክ እንደ ስታክ ማርኬት የሚመጣውን ትርፍ ካላስተዋል በስተቀር በአገር ጉዳይ ላይ አይሳተፍም።

ምሁሩም ሆን እኛም መሃይሞቹ ብዙ ያጠፋነው ስህትት ስለመኖሩ መካድ አይገባንም። ያለፈውን ስህተት ማንሳቱ ለስድብ ሳይሆን ካለፈው ስህተታችን ጠቃሚ ትምህርት ለመውሰድ ያስችለናል በማለት ነው።

የምርጫው ሰሞን ቅንጅቱ የህብረቱን ምክር ማዳመጥ የግድ ነበረበት። ምክንያቱም በህብረቱ ውስጥ የፖለቲካውን ውጣ ውረድ በተግባር የሚያውቁ የተመክሮ ባለባቶች አሉበትና። ችግር የተገባው የዘድሮው ዶክተር የጥንቱን ዶክተር ላለማዳመጥ፤ የዘ ድሮው ፖለቲከኛ የቀድሞዎቹን የፖለቲካ መሪዎች ያለማዳመጥ ብቻ ሳይሆን ማጣጣልም መያዙ ነው ። ትምክህትና ንቀትም አሉበት። አብረን እንስራ ሲባሉ እምቢኝ አሉ። እንኳን ምክር ሊቀበሉ ቀርተው ከወዳጅነት ይልቅ በጠላትነት ከመፈረጁ ላይ አዘነበሉ። አብሮ ላለመስራት በድብቅ ሳይሆን በገሃድ አስታወቁ። ህዝቡ የሚለግሰውን መዋጮ 70 ከመቶ ለኛ መሆን አለበት ብለው ቡራ ከረዮ መቱ። እነሱ ሙሉ ኢትይጵያዊ እኛ የህብረቱ ደጋፊዎች ሲሶ ኢትዮጵያዊ ሆን። ጉድ አልን፤ መቼም ጉድ አንድ ሰሞን አይደልም። የዳበረውን ምክራችንን ንቀው ጉዘውን ዘለቁት። ሂደው ሂደው ግድግዳ ተጋጭተው ጠበቁን። ምናልባት ህብረቱም ሆነ ቅንጅቱ አሁን አንቆ ከያዛቸው ችግር መውጣት ከቻሉ የተቀራረበና የተቀናበረ ትግል ማካሄድ የግድ ይጠበቅባቸዋል። ያለፈውን ስህተት ሰርተን ለወያኔ ትንፋሽ አንስጠው።

ዛሬ ብዙም የማይወራለት ኤኤፈዲ(AFD) ስለተባለው ክፉ ተንኮል ኢትዮጵያዊው ሁሉ ማወቅ ይገባዋል። ይህ የትግል እቅድ ዳግም ኢትዮጵያ የምትባል አገር ላለማየት የተሸረበባት ሴራ ነበር ። ሻቢያ ብሎ ለኢትዮጵያ ደህንነት ተቆርቋሪ ላለፉት 40 አመታትም አላየነውም። ይህ የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው የሚለውን አደናጋሪ የጮሌዎችን የፖለቲካ አባባል ለመረዳት ባለመቻላቸው እነ ጵጌና መዋ ቅንጅቱን በቀላሉ ከማይወጣው መቀመቅ ውስጥ ዘፍቀውታል። አሁንም ይህን አጥፊ ሳዳን ትክክል ነው የሚሉ እንዳሉ ይታያል። እኝ ያኔም አልተሳሳትንም አሁንም አንሳሳትም።

ዛሬ ተቃዋሚው ቡድን ዋነኛ ጠላቱን የዘነጋ ይመስላል። ወያኔን ከምንታገል ይልቅ ዛሬ የህዝባዊው ክፍል ባስመሳዮች እየታመሰ ይገኛል። አንዳንድ ድርጅቶችና የዘ ድሮ አንጃዎች ወያኔ አትበሉ የሚለውን ምክራቸውን ስንሰማ መንገዳቸው ወዴት ስለመሆኑ ለማወቅ ወደ የፖለቲካ ምሁር መሄድ አይገባንም። በተለይ በተለይ ከተኮላሸው ምርጫ ወዲህ ያብዛኛው ተቃዋሚ ድርጅቶች ተልእኮ በትንሽ ሳይሆን በብዙ ተቀይሮ እንዲያውም ከወያኔ በላይ የጠነከሩ የህዝብ ጠላት ሆነው ህዝቡን እያደናገሩ ትግሉንም እያውውገረገሩ እየተመለከትነው ነው።

ዛሬ የኢትዮጵያ ህዝብ የጠላት ብዛት ከመቁጠር ይልቅ ወዳጁን መቁጠሩ ይቀላል። ጠላቷማ በርክቷል። ወዳጅ ናቸው የሚባሉትም በጣት የሚቆጠሩ ድርጅቶችን በውል ወዳጅ ስለመሆናቸውም ለመለየት ተቸግረናል። አናሳ የሆኑት የኢህአፓና የቅንጅት አንጃዎች ራሳቸውን ከዋናው ድርጅት ፈልቅቀው ወጥተዋል። የብዙሃኑን ድርጅት ስም ፡ ልሳን፡ ንብረት በሽፍታነት ይዘው አለቅም ብለዋል። ትግላቸው ከወያኔ ሳይሆን ጥለውት ከወጡት ድርጅቶች ጋር ሆኗል። የሰላም ትግል ቦታ በለለው ባሁኑ ጊዜ ስለሰላሙ ትግል ብቻ ሳይታክቱ የሚሰብኩትን ያንጃውን መሪ እንዴት ነው የምንመለከታቸው? ለኢትዮጵያ ህይወት መጥፊያ የሆነውን AFD የተወሰኑ ሳጠኛ ያንድ ክንፍ የቅንጅት አንጃዎች ሲፈርሙ ህዝባችን እንዴት ይመለከታቸዋል? እነዚህ አንጃዎች ለምን በዚህ ወሳኝ የትግል ወቅት ብቅ ማለት ፈለጉ? ዛሬ ልዩነትን አቻችሎ ለህዝብ አለኝታ መሆን ነው የሚገባው ወይስ ድርጅትን መከፋፈል?

ያለፈውን ስህተት ደግሞ ደጋግሞ ማንሳት ሞራልን ለማዳሸቅ ሳይሆን ሌላ ተመሳሳይ ስህተት እንዳንደግም ትምህርት እንዲሆነን ነው። የተቃዋሚውን ጎራ ማጥራትና ሀቀኛ የሆኑትን ማጠናከር የህዝቡ ተቀዳሚ ተግባሩ መሆን አለበት። ልፍስፍ ወይም ታማኝ ተቃዋሚዎችን ህዝቡ ድጋፉን መንሳት አለበት። ሃቀኛ ተቃዋሚ ሃይሎች የተጠናከረ **ግንባር** መፍጠርና ትግላቸውን ማቀናጀት አለባቸው። ጊዜ የለንም። ፈጣን መሆን አለብን።



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com